**የበልግ 2021 የድንበር ሂደት ፡- የድኅረ ማጽደቅ ማሳወቂያ ደብዳቤ በ46140፣ 48150፣ 48280፣ 48281 እና 48290 ነዋሪ ለሆኑ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ቤተሰቦች**

ዲሴምበር 10 ቀን 2021

ውድ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ቤተሰቦች፡-

የትምህርት ቤቱ ቦርድ በዲሴምበር 2 ቀን 2021 ባካሄደው ስብሰባ ከኦገስት 2022 ጀምሮ ተፈጻሚነት የሚኖረውን የበልግ 2021 የድንበር ማሻሻያ በማጽደቅ ድምጽ ሰጥቷል፡፡

የ46140፣ 48150፣ 48280፣ 48281 እና 48290 የዕቅድ ዩኒቶች ከ2022-23 የትምህርት ዘመን ጀምሮ ከገንሰተን ወደ ጄፈርሰን መካከለኛ ትምህርት ቤት ተመድበዋል፡፡ ይህ ለውጥ ለሁሉም አዲስ ገቢ 6ኛ ክፍል ተማሪዎች (በ2021-22 የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች) እንዲሁም ከላይ በተዘረዘሩት የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ ነዋሪ ለሆኑ የወደፊት አዲስ ገቢ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ በዱዋል ቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራም ወይም በሞንቴሶሪ ፕሮግራም ያሉ ተማሪዎች እነዚህን ፕሮግራሞች በገንስተን መካከለኛ ትምህርት ቤት መቀጠል ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ከላይ ከተዘረዘሩት የዕቅድ ዩኒቶች መካከል በአንዱ ነዋሪ የሆኑ እና በአሁኑ ጊዜ በገንስተን የሚማሩ ወይም ከጁን 17 ቀን 2021 በፊት በገንስተን የሚገቡ የ6ኛ ወይም 7ኛ ክፍል ተማሪዎች የ8ኛ ክፍል ትምህርታቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ በገንስተን መቀጠል ወይም በ2022-23 አዲስ በተመደቡበት የአካባቢው ትምህርት ቤት (ጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) መቀጠል ይችላሉ፡፡

***ወንድምና እህቶች፣ እና የትራንስፖርት መረጃ***

- ***ወንድሞችና እህቶች፡-*** በገንስተን የ6ኛ -7ኛ ክፍል ተማሪዎች ወንድሞች/ እህቶች የሆኑ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ ከላይ ከተዘረዘሩት ዩኒቶች በአንዱ ነዋሪ የሆኑ በ2022-23 የትምህርት ዘመን ወደ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ከታላላቅ ከወንድሞቻቸው ወይም እህቶቻቸው ጋር በገንስተን አብረው መማር እንዲችሉ ሊዘዋወሩ ይችላሉ፡፡ ለእነዚህ ቤተሰቦች ራሱን የቻለ ደብዳቤ እና ቅጽ ይላካሉ፡፡

- ***ትራንስፖርት ፡-*** የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከላይ በሚገኙት የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ ያሉ ነገር ግን በእግር ከሚደረስበት ዞን ውጪ ነዋሪ ለሆኑ ተማሪዎች ጄፈርሰን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ (አዲስ የተመደበ የአካባቢው ትምህርት ቤት) ትራንስፖርት ያቀርባል፡፡

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ ተመራጩ ጥያቄዎን የማቅረብ ዘዴ በengage@apsva.us ኢሜል ማድረግ ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-2481 የዕቅድ እና ግምገማ ክፍልን ማነጋገር ነው፡፡ የበልግ 2021 የድንበር ሂደትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ከዚህ የሚከተለውን ሊንክ ይጎብኙ፡- https://www.apsva.us/engage/fall-2021-boundary-process፡፡

አመሰግናለሁ፣

ሊሳ ስቴንግል
የዕቅድ እና ግምገማ ዳይሬክተር
አርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች